የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
Ethiopian People's Patriotic Front
ለኢትዮጵያ አንድነትና ዲሞክራሲ
Unity & Democracy for Ethiopia

**Friday, 23 July 2010 12:43**

*የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ከግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ጋር ውይይት አደረገ።*

*የኢህአግ የውጭ ጉዳይ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትከግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ጋር ውይይት ያደረጉት በትናንትናው እለት ማለትም ሐምሌ 15ቀን 2002 እ.ም ሲሆን፣ድርጅቱ ሃላፊነት ከሰጣቸው ጊዜ ጀምሮየተሰሩ ስራዎችንና የገጠማቸውን ችግሮች በዝርዝር አስረድተዋል።*

*የውጭ ጉዳይ ኮሚቴው አያይዞም በቅርቡ በለንደንና በዋሽንግተን ዲሲ ህዝባዊ ስብሰባ እንደሚያደርግ አስታውቆ የድርጅቱ ድጋፍ እንዳይለየውም ጠይቋል።*

*የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ስራ አስፈፃሚ አባላት በበኩላቸው በውጭው አለም ተንቀሳቅሰው ለድርጅቱ በተለያየ መልኩ ድጋፍ እንዲያደርጉ መመደባቸውን አስታውቀ እስካሁን አመርቂ ስራ እንዳልተሰራና ወደፊትም በተጠናከረ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ አስታውቋል።*

*አያይዘውም የድርጅቱ ስራ አስፈፃሚ ድርጅቱ እስካሁን ባለፉባቸው የትግል አመታት በይበልጥ በውጭው አካል ከፍተኛ እንቅፋት የነበረበትና አሁንም ያለበት መሆኑን አስታውቀ በውጭው አለም የተመደቡ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት የድርጅቱን ህግና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አድረው እንዲሰሩም አሳስቧል።*

*በማስከተልም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን እያደረገና ከፍተኛ የበላይነትም እየተቀዳጀ መሆኑን የገለፁት የስራ አስፈፃሚ አባላት ወያኔን በመቃወም እየተፋለሙ ካሉ ድርጅቶች ጋረብሮ ለመስራት ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ሲሆን፣ በኮሎኔል አለበል አማረ የሚመራው አማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ/ አዴሐን/ ጋር ውህደት የማድረግ ደረጃ ላይ የደረስ በመሆኑና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ባለው ሁኔታ ድርጅቱ በቅርቡ ሃገራዊ ስብሰባ የሚጠራ መሆኑን በማስታወቅ በውጭው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪውን በማስተላለፍ በቅርቡ የሚደረገውን ይህን አገራዊ ስብሰባ በማስመልከት ያለውን ዝርዝር ሁኔታ በድርጅቱ ድረ-ገፅ የሚያወጣ መሆኑንም አስታውቋል።*

*የኢህአግ ስራአስፈጻሚ ኮሚቴ አስከትሎም በየካቲት 23 ቀን 2002 እ.ም ባካሄደው ጉባኤ 17 የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት በውጭው አለም እንዲሰሩ የመደበ ሲሆን፣ እነዚህ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ደግሞ በሶስት ስራ አስፈፃሚዎች ማለትም 1- ኮሎኔል ጌትነት ሊበን 2-አቶ ዘውድአለም ከበደ በም/ሊቀመንበርነት 3-አቶ ጥላሁን ገላው በዋና ጸሓፊነት መድቦ የላካቸው መሆኑን በመጠቆም በነዚህ ግለሰቦች ግለሰቦች አመራር ሰጭነት ውጭ የሚደረጉ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ ህጋዊ አለመሆኑን በመግለጽ በውጭው አለም የሚገኘው ኢትዮጵያዊም ከነናቸው እንዲቆም ጥሪውን አስተላልፏል።*

*የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ስራ አስፈፃሚ*